የአውሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ምክር ቤት
The Council of European and African Kinijit Support Groups
1 Crowndale Road London NW1 1TU UK Tel: +44 (0) 20 7168 9893 Email: euafkinijit@googlemail.com

ኦገስት 9 ቀን 2007

**የቅንጅት ከፍተኛ የልዑካን ቡድን በአዉሮፓ ጉብኝት ያደርጋል::**

የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ ከፍተኛ የልዑካን ቡድን እ. ኤ. አ ከነሐሴ 20 ቀን 2007 ጀምሮ በአዉሮፓ የሥራ ጉብኝት ያደርጋል:: የልዑካን ቡድኑ አባላት በቅርቡ ከእስር የተፈቱት የፓርቲዉ ከፍተኛ አመራር አባላት ሲሆኑ፣ እነርሱም፣

1. አቶ ሙሉነህ ኢዩኤል
2. ዶ/ር ያዕቆብ ኃይለማርያም
3. አቶ ዓባይነህ ብርሃኑ
4. አቶ ክፍሌ ጥግነህ
5. አቶ አስቻለዉ ከተማ ናቸዉ::

የልዑካን ቡድኑ በተለያዩ የአዉሮፓ አገሮች በመዘዋወር የድርጅቱን አባላትና ደጋፊዎች፣ እንደዚሁም የኢትዮጵያን ወዳጆችና ማህብረሰቦችን ያነጋግራል:: የጉብኝቱ ዝርዝር ፕሮግራምና ተዛማጅ መረጃዎች በሂደት የሚገለጹ ይሆናል::

ካዉንስሉ ጉብኝቱ የተሳካ እንዲሆን አስፈላጊዉን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ሲሆን፣ የቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች፣ አገር ወዳድ ዜጎችና አፍቃሬ ዴሞክራሲ ሃይሎች ሁሉ ለተልዕኮዉ ስኬታማነት የተለመደዉን ቅንነት የተሞላዉ ድጋፍና እርዳታ እንዲያደርጉ ከወዲሁ ያሳስባል::

ሰላምና ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ!!!

ጽ/ቤቱ